## 1.2 ከድርጅታዊ ጥንካሬ አንፃር የቅንጅቱ አባል ድርጅቶች አሰላለፍ

ባለፈው ሳምንት ፅሑፌ ዶ/ር ብርሃኑ አመጣን የሚሉት አዲስ አስተሳሰብና ራዕይ መሠረተ ቢስ መሆኑን ለማሳየት ሞክሬአለሁ፡፡ በዛሬው ፅሑፌ ደግሞ ዶ/ር ብርሃኑ በመፅሐፋቸው ውስጥ በምርጫ 97ዓ.ም ቅንጅቱ "ጠንካራ" ድርጅት ሆኖ መቅረብ የቻለው በዋናነት በእርሳቸውና በቀስተዳመና ምክኒያት እንደሆነ አድርገው በሰፊው ያቀረቡት ሃተታ ምን ያህል መሠረተ ቢስ እንደሆነ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡

ቅንጅት በተመሠረተበት ወቅት በዋናነት የድርጅት መልክና ቅርፅ ይዘው ይንቀሳቀሱ የነበሩት መኢአድና ኢዴአፓ-መድህን ናቸው፡፡ በወቅቱ ከተመሠረተ ሁለት ዓመት አስቆጥሮ የቅንጅቱ 3ኛ አባል ድርጅት የነበረው ኢዴሊ በወቅቱ ምንም ዓይነት የሚታይና የሚዳሰስ ድርጅታዊ እንቅስቃሴ ያልነበረው ከመሆኑም በላይ የድርጅቱ መሪና አመራሮች እነማን እንደሆኑ እንኳ በውል አይታወቅም ነበር፡፡ የቅንጅቱ 4ኛ አባል ድርጅት ቀስተ ዳመና ከቅንጅቱ ምስረታ በፊት ምንም አይነት ድርጅታዊ እውቅናም ሆነ እንቅስቃሴ ያልነበረው ድርጅት ሲሆን ቅንጅቱ በተመሠረተበት ወቅት በውስጡ የነበሩት አባላት ከ12 ያልበለጡ ግለሰቦች ነበሩ፡፡ እነዚህም ግለሰቦች በወቅቱ በግልፅ ይናገሩ የነበረው ሚናቸው ሁለቱን ዋና ዋና ድርጅቶች መኢአድንና ኢዴአፓ-መድህንን በጋራ እንዲሰሩ ለማድረግ የሽምግልና ሚና ከመጫወት ያለፈ እንዳልሆነና እንደ ድርጅት ወደፊት የመጠናከርም ሆነ የመስራት ፍላጐት የሌላቸው መሆኑን ነበር፡፡

መኢአድ በወቅቱ ከ500 ሺ የፓርቲ አባላትና ከ200 በላይ ቅርንጫፍ ቢሮዎች በአጠቃላይ በአገሪቱ የነበረው ሲሆን፣ ኢዴአፓ-መድህን አርባ ሺ የሚጠጉ አባላትና 22 ቅርንጫፍ ቢሮዎች ነበሩት፡፡ የአባላትና የቢሮ ቁጥርን ብዛት እንደ አንድ ዋና የፓርቲ ጥንካሬ መመዘኛ በመውሰድ መኢአድ እራሱን ከኢዴአፓ-መድህን የበለጠ ጠንካራ ፓርቲ አድርጐ ይቆጥር ነበር፡፡ እውነታውን ወደ ውስጥ ጠለቅ ብለው እስከሚያውቁት ድረስ ይህንን የመኢአድ ጠንካራ ድርጅትነት የቀስተ ዳመና ሰዎችም ይጋሩት ነበር፡፡ በእርግጥ መኢአድና ኢዴአፓ-መድህን በአባላትና በቅርንጫፍ ቢሮዎች ቁጥር ረገድ ያላቸው መጠን በጣም የተራራቀ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ የሆነው ሁለቱ ድርጅቶች በድርጅታዊ ጥንካሬአቸው ያን ያህል የተራራቁ ሆነው ሳይሆን ይከተሉት የነበረው የአደረጃጀት ስልት በጣም የተለያየ ስለነበር ነው፡፡ ሁለቱ ድርጅቶች የዚህ አይነት የስልት ልዩነት እንደነበራቸው የቅንጅቱ አባል ድርጅቶች እጩዎችን ለማቅረብ ባደረጉት የእርስ በርስ ድርድር ወቅት በግልፅ መታየቱን በተለባበሰና ይሉኝታ ባጠላበት ሁኔታም ቢሆን ዶ/ር ብርሃኑ በሚከተለው መልክ መፅሐፋቸው ውስጥ አስፍረውታል፡፡

"---ሁለቱ ድርጅቶች በየራሳቸው ረቂቅ የመስፈርት ሃሣብ እንዲያመጡ ተጠይቀው ይዘው የመጡት በጣም ሰፊ ልዩነት ስለነበረው ከመስፈርቱ ጀርባ የሚደረግ ትግል እንዳለ ለማወቅ ጊዜ አልወሰደብንም፡፡ በኢዴአፓ-መድህን በኩል የቀረበው ረቂቅ መስፈርት 'የትምህርት ደረጃ' ለሚል መለኪያ ትልቁን ነጥብ ይሰጥና (ወደ 80% ግድም) ለሌሎች አስፈላጊ መለኪያዎች በጣም ትናንሽ ነጥቦች ይሰጣል፡፡ በአንፃሩ በመኢአድ በኩል 'የድርጅት ጥንካሬ' ለሚል መለኪያ ትልቁን ነጥብ (ወደ 40%) ይሰጥና ለትምህርት ደረጃ ከ20% ያልበለጠ ነጥብ ይሰጣል፡፡" (ገፅ 235)

ይህ ከዚህ በላይ የጠቀስኩት የዶ/ር ብርሃኑ አባባል ሁለቱ ድርጅቶች ይከተሉት የነበረውን የአደረጃጀት የስልት ልዩነት በግልፅ የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ በመኢአድ በኩል ሁልጊዜ 'የድርጅት ጥንካሬ' ተደርጐ የሚቆጠረው የአባላትና የቢሮዎች ብዛት ሲሆን፣ በኢዴአፓ-መድህን በኩል ደግሞ እንደዋና 'የድርጅት ጥንካሬ' ተደርጐ የሚወሰደው መስፈርት የአባላት የፖለቲካ ግንዛቤና የትምህርት ደረጃ (እውቀት) እንደነበር በግልፅ

ይታያል፡፡ ነገር ግን ዶ/ር ብርሃኑ ከዚህ የተለባበሰ አገላለፃቸው አለፍ ብለው እውነቱን በተሻለ ሁኔታ ለአንባቢ ለማቅረብ ድፍረትም ፍላጐትም ያላቸው አይመስሉም፡፡ ስለ ኢዴአፓ-መድህን ጥንካሬ ከዚህ በተሻለ ሁኔታ ማውራት የራሣቸውንና የቀስተ ዳመናን ሚና ስለሚያደበዝዝባቸው በሁሉም የመፅሐፋቸው ክፍል ኢዴአፓ-መድህንን በተመለከተ የሚያቀርቧቸው ሃሣቦች እጅግ የተለባበሱና የተንሻፈፉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ከብዙ ውይይትና መቻቻል በኋላ በእጩዎች ማቅረቢያ መስፈርቱ ላይ ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ በተደረገው ድርድር በቅንጅቱ ውስጥ የየአንዳንዱ አባል ድርጅት የእጩዎች ብዛት ድርሻ ምን ያህል እንደነበር ሆን ብለው ሳይገልፁት አልፈዋል፡፡ እውነታውን በግልፅ ከማስቀመጥ ይልቅ ዶ/ር ብርሃኑ የድርድሩን ሂደትና ውጤት በተድበሰበሰ አገላለፅ በሚከተለው መልኩ አስፍረውታል፡፡

"---በኢዴአፓ-መድህን በኩል ሁልጊዜ ለድርድር የሚመጣው ልደቱ ነበር፡፡ ልደቱ በደንብ አስቦና ተዘጋጅቶ፣ እንደ ጥሩ ቼዝ ተጫዋች የሚወስደውን የመጀመሪያ እርምጃም ሆነ ሌላው አካል ሊሰጥ የሚችለውን መልስ ከግንዛቤ አስገብቶ፣ ከዚህ ውሳኔም በኋላ ድርድር ቢኖር ለዚያ ድርድር የሚጠቀመውን አስልቶ በሙሉ አቅሙ ማሸነፍን ብቻ ማዕከል አድርጎ ይንቀሳቀሳል፡፡" (ገፅ 239)

ዶ/ር ብርሃኑ ስለ ኢዴአፓ-መድህን የመደራደር አቅም ይህንን ካሉ በኋላ ወረድ--- ብለው ደግሞ ስለ መኢአድ የሚከተለውን ይላሉ -፡፡

"--- በመኢአድ በኩል የነበረው አብዛኛው የየዋህነት አካሄድና በቅንጅቱም ላይ በተለይም በሁለቱ ድርጅቶች መሃከል በነበርነው ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ የነበራቸው እምነት በአንድ በኩልና፣ በድርጅታቸው 'ጠንካራነት' ላይ የነበራቸው ጭፍን እምነት ለልደቱ ጠንቃቃ፣ ዒላማውን አስቀድሞ ያሰላ የብልጠት አካሄድ የሚመጥን አልነበረም፡፡ ስለዚህ በድርድሩ ውጤት በምንም ዓይነት የመኢአድ ሰዎች የሚስማሙ አልሆኑም፡፡" (ገፅ 240)

ይህ የዶ/ር ብርሃኑ አባባል እንዳለ በጥሬው ቢወሰድ ሊያስተላልፈው የሚችል ቁምነገር መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ቢያንስ ሦስት መሠረታዊ ግድፈቶች አሉበት፡፡ የመጀመሪያው የመዋሸት ችግር ነው፡፡ ይኸውም ዶ/ር ብርሃኑ - "በኢዴአፓ-መድህን በኩል ሁልጊዜ ለድርድር የሚመጣው ልደቱ ነበር" በማለት የገለጹት ፍፁም ሃሰት ነው፡፡ እኔ አንድም ቀን ከላይ በተጠቀሰው የቅንጅት መስፈርት መሠረት በተደረገው በማንኛውም ድርድር ላይ ተገኝቼ አላውቅም፡፡ በመስፈርቱ መሠረት በተደረገው ከሳምንት በላይ የፈጀ ድርድር ኢዴአፓ- መድህንን በመወከል የተደራደሩት የእጩ ምልመላና ምደባ ንዑስ ኮሚቴ አባል የነበሩት ሰዎች ሲሆኑ በዚህም መሠረት በአማራ፣ በትግራይ፣ በአፋርና በቤንሻንጉል ክልል የሚገኙ እጩዎቻችንን በተመለከተ አቶ አብዱራህማን አህመዲን፣ አዲስ አበባንና ደቡብ ክልልን በተመለከተ አቶ መስፍን መንግሥቱ፣ ኦሮሚያ እና ሐረሪን በተመለከተ አቶ ታምራት ታረቀኝ ሲሆኑ ጋንቤላና ሱማሌ ክልልን በተመለከተ ኢዴአፓ-መድህን በቅንጅቱ ውስጥ ብቸኛ እጩ አቅራቢ ስለነበር ድርድር አልተካሄደም፡፡ እኔ የእጩዎች ድርድር ላይ የተገኘሁት መኢአድ የድርድሩን ውጤት አልቀበልም ብሎ ካፈነገጠ በኋላ ከመስፈርቱ ውጭ የመኢአድን ጥያቄ ለማስተናገድና ቅንጅቱን ከመፍረስ ለማዳን ተብሎ በተካሄዱት ድርድሮች ላይ ብቻ ነበር፡፡

ሁለተኛው ችግር ዶ/ር ብርሃኑ ኢዴአፓ-መድህን ድርድሩን ያሸነፈው በአቀረባቸው እጩዎች ጥራት ሳይሆን በተደራዳሪዎቹ (በልደቱ) የብልጠት አካሄድ እንደሆነ አድርገው ማቅረባቸው ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ አንድ የፖለቲካ ሰው ለአንድ አይነት ድርድር ሲቀርብ ሞኛሞኝ ሆኖ ከመገኘት ይልቅ ድርድሩን ለማሸነፍ የሚያበቃ ብልጠት ይዞ ቢቀርብ ነውርነት ያለው አይመስለኝም፡፡ ነገር ግን ድርድሩ የተካሄደው አስቀድመው

በተቀመጡ መመዘኛዎችና ለእነዚህ መመዘኛዎችም አደራዳሪዎች ምን ያህል ውጤት (Mark) መስጠት እንዳለባቸው አስቀድሞ ተወስኖ የተቀመጠ ስለነበር ዶ/ር ብርሃኑ እንደሚሉት ማንም ድርድሩን በተለየ ብልጠት የሚያሸንፍበት ምክኒያት አልነበረም፡፡ ሦስተኛው ችግር ዶ/ር ብርሃኑ ከድርድሩ በኋላ በተገኘው ውጤት የመኢአድና የኢዴአፓ-መድህን ድርሻ ምን ያህል የተራራቀ እንደነበር ደፍረው ሊያቀርቡት ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡ የነበረውን የውጤት ልዩነት በግልፅ በማሳየት አንባቢ በሁለቱ ድርጅቶች በኩል ቀድሞውንም የነበረውን የጥራት ልዩነት እንዲገነዘብ ከማድረግ ይልቅ በደፈናው “መኢአድ ውጤቱን ሊቀበለው አልቻለም” በማለት አድበስብሰው ሊያልፉት ሞክረዋል፡፡ ነገር ግን ይህ የደርድር ውጤት በአንድ በኩል ሁለቱ ድርጅቶች (መኢአድና ኢዴአፓ-መድህን) ይከተሉት የነበረውን የአደረጃጀት ስልት ልዩነት በግልፅ የሚያሳይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ሲል የመኢአድና የቀስተደመና ሰዎች መኢአድ በጣም ጠንካራ ድርጅት እንደሆነና በአንፃሩ ኢዴአፓ-መድህን ደካማ የከተማ ፓርቲ እንደሆነ አድርገው ሲያወሩት የነበረው ወሬ መሠረተ ቢስ እንደነበረ ያረጋገጠና በአጠቃላይም በቅንጅቱ ውስጥ የነበረውን የአባል ድርጅቶች የድርጅታዊ ጥንካሬ ደረጃ በግልፅ የሚያሳይ ስለሆነ ዶ/ር ብርሃኑ ሊገልፁት ያልፈለጉትን የድርድር ውጤት እኔው እራሴ እንደሚከተለው በጥቅሉ እገልፀዋለሁ፡፡

ከሳምንት በላይ ቀንም ሌሊትም የተደረገው ድርድር ተጠናቆ ውጤቱ ሲገለፅ ቅንጅቱ በአገር ደረጃ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከሚያቀርባቸው እጩዎች ውስጥ 68% ገደማ የሚሆኑት ኢዴአፓ-መድህን ያቀረባቸው እጩዎች መሆናቸው ታወቀ፡፡ ከዚህ ውስጥ በተለይም ደግሞ ቅንጅቱ በአጠቃላይ የተሻለ የመመረጥ እድል ይኖረዋል ተብሎ በሚገመትበት በአማራ ክልል ከ80% በላይ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ከ85% በላይ ያሸነፉት የኢዴአፓ-መድህን እጩዎች መሆናቸው ሲታወቅ ከፍተኛ ድንጋጤና የሞራል ድቀት የደረሰበት መኢአድ ውጤቱን አልቀበልም ብሎ አፈነገጠ፡፡ በዚያ የድርድር ውጤት መሠረት ቀስተዳመናና ኢዲሊ በጋራ በቅንጅቱ ውስጥ የነበራቸው አጠቃላይ ድርሻ ከ4% የበለጠ አልነበረም፡፡ በወቅቱ ይህ ውጤት መኢአዶችን ብቻ ሳይሆን ስለ መኢአድ ጠንካራ ድርጅትነት የተሟላ እምነት የነበራቸውን የቀስተዳመና ሰዎችንም ጭምር ያስደነገጠ ነበር፡፡ መኢአድ ይህንን አስቀድሞ በተቀመጠ መስፈርት መሠረት የተገኘን ውጤት አልቀበልም ብሎ ያፈነገጠው ቀደም ሲል በሰፊው ሲያስወራ እንደበረው ከኢዴአፓ-መድህን የበለጠ ጠንካራ ድርጅት አለመሆኑ ስለተረጋገጠና በዚህ ምክኒያት ሃፍረት ስለደረሰበት ብቻ አልነበረም፡፡ ይልቁንም ዋና ምክኒያት የነበረው በዚያን ወቅት እነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻዎል በምርጫው ቅንጅት ኢህአዴግን አሸንፎ ለመንግሥትነት ስልጣን እንደሚበቃ ቅንጣት ያህል ጥርጥር ስላልነበራቸው - ቅንጅቱ እነዚህን በድርድሩ ውጤት የተገኙትን እጩዎች ይዞ ለውድድር ከቀረበ በኋላ በምርጫው ቢያሸንፍ በአዲሱ የቅንጅት መንግሥት በፓርላማ ውስጥ አብዛኛውን መቀመጫ የሚያገኙት የኢዴአፓ-መድህን አባላት ስለሚሆኑና ይህም ከኢንጂነር ኃይሉ ሻዎል የተለየ የራሳቸውን ጠቅላይ ሚኒስትር ለመምረጥ እድል ያገኛሉ የሚለው ስጋት ስለነበራቸው ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን ስጋታቸውን ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት መኢአዶች በምርጫው ከኢዴአፓ-መድህን የበለጠ ቁጥር ያለው እጩ ካላቀረብን በስተቀር ከቅንጅቱ ጋር አብረን አንቀጥልም የሚል አቋም በመያዝ እራሳቸው አስቀድመው በተስማሙበት መስፈርት መሠረት የተገኘውን የድርድር ውጤት አንቀበልም ብለው አፈነገጡ፡፡ እንዲህ አይነት ግልፅ የአፍራሽነት ሚና ይዞ መኢአድ ስምምነቱን አፍርሻለሁ ሲል -ከማንም በላይ ለመርህና ለእውነት እንቆረቆራለን የሚሉት እነ ዶ/ር ብርሃኑ የመኢአድን አፍራሽነት ለሕዝብ ለማጋለጥ ወይንም በመኢአድ ላይ ጫና ፈጥሮ ስምምነቱን እንዲያከብር ማድረግን አልነበረም የመረጡት፡፡ ይልቁንም መኢአድ የሚያቀርበውን ጥያቄ ሁሉ በፀጋ በመቀበል “ቅንጅቱን ከመፍረስ አድኑት” እያሉ በልመናና በማባበል ተፅዕኖ ማድረግ የሚፈልጉት በኢዴአፓ-መድህን ላይ ሆነ፡፡ ኢዴአፓ-መድህንም በአንድ በኩል ከእንዲህ አይነት ለራሱ ስምምነት ተገዥ ያልሆነ ድርጅት ጋር አብሮ በመጓዝ ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል አበክሮ እያስገነዘበ፣

በሌላ በኩል ደግሞ በወቅቱ ከነበረው የሕዝብ ስሜትና ተነሳሽነት አንፃር ኢ.ዴ.አ.ፓ-መድህን ተጐድቶ ቅንጅት ከመፍረስ ቢ.ድን ይሻላል በሚል አመለካከት (በእርግጥ ዛሬ ላይ ሆነን እራሳችንን ስንገመግም ይህ አይነቱ አቋማችን ስህተት ነበር) የመኢ.አድን አግባብ ያልሆነ ጥያቄ አሜን ብለን ተቀበልን፡፡

በዚህ የመኢ.አድ ጥያቄ መሠረት በአዲስ አበባና በተለያዩ ክልሎች ኢ.ዴ.አ.ፓ-መድህን ለመኢ.አድ በርካታ የምርጫ ክልሎችን እንዲለቅ ሲ.ደረግ በጣም በሚያስገርም ሁኔታ የድርድሩ መስፈርትና ውጤት ሙሉ በሙሉ እንዲሠረዝ ተደርጐ አማራ ክልልን ሙሉ በሙሉ ሁለቱ ድርጅቶች እኩል በኩል እንድንካፈል ተደረገ፡፡ በዚህ ምክኒያት በርካታ የኢ.ዴ.አ.ፓ-መድህን ዲግሪና ዲፕሎማ ያላቸው እጩዎች ማንበብና መፃፍ ብቻ በሚችሉና ምንም አይነት የፖለቲካ ብቃት በሌላቸው አርሶ አደሮችና ቄሶች እንዲለወጡ ተደረገ፡፡ ይህም ከሆነ በኋላ መኢ.አዶች አጠቃላዩ የእጩዎቻቸው ቁጥር ከ50 በመቶ በላይ ሊሆንላቸው ስላልቻለ ከአራት ጊዜ በላይ እንደገና ስምምነታቸውን እያፈረሱና ከቅንጅቱ ልንወጣ ነው በማለት እያስፈራሩ በርካታ ተጨማሪ ቦታዎችን ከኢ.ዴ.አ.ፓ-መድህን ነጠቁ፡፡ ለምሳሌ ያህል አዲስ አበባ ከተማ ላይ የነበረውን ሁኔታ ለማየት ብንሞክር - በድርድሩ ሂደት ኢ.ዴ.አ.ፓ-መድህን በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙት 23 የምርጫ ክልሎች ውስጥ በ18ቱ አሸንፎ በ2ቱ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር እኩል የወጣ ሲሆን በቀሪዎቹ ሦስት ወረዳዎች ብቻ ተሸንፏል፡፡ በዚህ ውጤት መሠረት ኢ.ዴ.አ.ፓ-መድህን ከሌሎቹ ጋር እኩል በወጣባቸው ሁለት የምርጫ ክልሎች ውስጥ አንዱን ለቆ ሌላኛውን ቢ.ያገኝ በአጠቃላይ ከ23ቱ ወረዳዎች ውስጥ የአሸነፈባቸው ወረዳዎች 19 ይሆናሉ፡፡ ነገር ግን ከድርድሩ ውጤት በኋላ በተደረጉት ድርድሮች ወረዳ 23ን ለኢ.ንጂነር ኃይሉ፣ ወረዳ 18ን ለሻለቃ አድማሱ፣ ወረዳ 17ን ለኢ.ንጂነር ግዛቸው፣ ወረዳ 7ን (በወረዳ 26 ምትክ) ለአቶ በድሩ አደም፣ ወረዳ 24ን ለዶ/ር በፍቃዱ፣ ወረዳ 6 እና 25ን ለኢ.ዴ.ሊ. ሰዎች ለቆ መጨረሻ ይዞት የቀረው 13 ወረዳዎችን ብቻ ሆነ፡፡ ምንአልባት እነዚህ ስማቸውን የዘረዘርኳቸው ሰዎች የትምህርት ደረጃቸውን ከፍተኛነት በማየት እንዴት ኢ.ዴ.አ.ፓ-መድህን ለነዚህ ሰዎች ቦታ ሊ.ለቅላቸው ቻለ? የሚል ጥያቄ ሊ.ያስነሳ ይችላል፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደጠቀስኩት የአቶ በድሩ አደም ቦታ በለውጥ የተገኘ ከመሆኑ በስተቀር ከኢ.ንጂነር ኃይሉ ሻዎል ጀምሮ ሌሎች ሰዎች በተቀመጠው የድርድር መስፈርት መሠረት በኢ.ዴ.አ.ፓ-መድህን እጩዎች የተሸነፉ ወይንም እኩል የወጡ ሰዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን ዶ/ር ብርሃኑ ኢ.ዴ.አ.ፓ-መድህንን ሊ.ያሳንስልኝ ይችላል ብለው የገመቱትን ብዙ ጥቃቅን ጉዳዮችን ሳይቀር በመፅሐፋቸው ውስጥ አካተው ሲ.ያስነብቡን ኢ.ዴ.አ.ፓ-መድህን ምን ያህል ጥቅሙን ያለ አግባብ አሳልፎ እየሰጠ ቅንጅቱን ከመፍረስ በማዳን ረገድ ያበረከተውን አስተዋፅኦ ለሕዝብ መግለፅ አልፈለጉም፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ የእኔን፣ የአቶ ሙሼንና የአቶ አብዱራህማንን ስም ምን ያህል አንባቢ.ን በሚ.ያሳስት ዘዴ ለመበከል ጥረት እንዳደረጉ በቀጣዮቹ የዚህ ፅሁፍ ክፍሎች የምመለስበት ስለሆነ አሁን ወደዋናው የተነሳሁበት ርዕሰ ጉዳይ ልመለስ፡፡

መኢ.አድ ከላይ በጠቀስኩት መልኩ በተደጋጋሚ ስምምነቱን እየጣሰ የማይገባውን የእጩዎች መጠን በእጁ ካስገባም በኋላ ከአፍራሽነት ሚናው አልተቆጠበም ነበር፡፡ የድርድር ሂደቱ ሙሉ በሙሉ በተጠናቀቀበትና በምርጫ ቦርድ እጩዎችን የማስመዝገቡ ሂደት በሚ.ጠናቀቅበት ዕለት እንደገና ቅንጅቱን የማፍረስ አቋም ይዞ ብቅ አለ፡፡ መኢ.አድ በዚህ ወሳኝ ወቅት ቅንጅቱን ለማፍረስ ያደረገውን ጥረት ዶ/ር ብርሃኑ በተሸራረፈ ሁኔታም ቢ.ሆን በመፅሐፋቸው ውስጥ በሚከተለው መልኩ አስፍረውታል፡፡

"--- የድርድሩ ውጤት በመኢ.አድ ተቀባይነት አጥቶ፣ ነገሩ ሁሉ ሊ.ፈርስ ሆነ፡፡ እኛ የድርድሩን ውጤት መሠረት አድርገን በኮሚ.ቴው በኩል ጠቅላላ የእጩዎችን ዝርዝር ለምርጫ ቦርድ ለማስተላለፍ መዘጋጀት ጀመርን፡፡ ቅንጅቱ ይህን በማድረግ ላይ እያለ መኢ.አድ በስራ አስፈፃሚ.ው በኩል አስወስኖ የራሱን የተለየ የምርጫ አርማ አዘጋጅቶ በሁሉም ወረዳ የሚ.ቀርቡትን የራሱን እጩዎች ዝርዝር ለምርጫ ቦርድ አቀረበ፡፡ ይህን

እርምጃ በመውሰድ በተግባር ቅንጅቱን የሚያፈርስ ተግባር ፈፀመ፡፡ ይህን ማድረጉን በሰማን ሰዓት የደረሰብን ድንጋጤ በእውነት ለማመን የሚቻል አልነበረም፡፡” (ገፅ 241)

በአለቀ ሰዓት መኢአድ ይህንን አይነት የአፍራሽነት ድርጊት ከፈፀመ በኋላ በጣም የተደናገጡት እነ ዶ/ር ብርሃኑ ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንዳደረጉት አሁንም ኢዴአፓ-መድህንን አስገድዶና አታሎ መኢአድ የፈለገውን እንዲያገኝ ከማድረግ የተለየ አማራጭ አልታያቸውም ነበር፡፡ ችግሩ በተፈጠረ ማግስት ዶ/ር ብርሃኑና ፕ/ር መስፍን ሰኞ ጧት እኔና አቶ ሙሼ አግኝተን እንድናነጋግራቸው ፕ/ር መስፍን ቤት ድረስ ቀጠሮ ሰጡን፡፡ በቀጠሮው ሰዓትና ቦታ ላይ አራታችን እንደተገናኘን ዶ/ር ብርሃኑ ለተፈጠረው ችግር መፍትሔ ነው ብለው ያመኑበትን ሃሣብ ተቀምጠው ሳይሆን ቆመው እየተንቆራጠጡ በሚከተለው መልኩ ለእኔና ለአቶ ሙሼ ገለፁልን -፡፡

“ስለመኢአድና ስለአቶ ኃይሉ ሻዎል በተደጋጋሚ ስትነግሩን የነበረው ሁሉ ትክክል መሆኑን አሁን በተግባር ማረጋገጥ ችለናል፡፡ ነገር ግን በዚህ መሠሪ ድርጅት አማካኝነት አሁንም ቅንጅቱ መፍረስ ስለሌለበት በኛ በኩል መፍትሔ አድርገን የደረስንበትን ሃሣብ ልንገልፅላችሁ ፈልገናል፡፡ እስካሁን ቅንጅቱ ተርፎ ከዚህ መድረስ የቻለው በእናንተ ታጋሽነት ነው፡፡ አሁንም ቅንጅቱን የማትረፍ እድል የሚገኘው በእናንተ እጅ ነው፡፡ እስካሁን ካደረጋችሁት የሚብስ ነገር ስለሌለ ዛሬ ከሰዓት በኋላ በሚደረገው የቅንጅቱ ምክር ቤት ስብሰባ መኢአድ እንድትለቁለት የሚጠይቃችሁን የምርጫ ክልል ሁሉ በፈቃደኛነት ልቀቁለት፡፡ እናንተ ይህን ካደረጋችሁ ያለጥርጥር መኢአድ ለምርጫ ቦርድ ያስገባውን ደብዳቤ እንዲሰርዝ ማድረግና ቅንጅቱን ከመፍረስ ማዳን ይቻላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ቅንጅቱን ካተረፍንና ለምርጫ ቦርድ አቤቱታ የማቅረቢያ ጊዜው የፊታችን እሮብ ከተጠናቀቀ በኋላ በኛ በኩል በማግስቱ ሐሙስ እለት የመጀመሪያው ስራችን የሚሆነው የቅንጅቱን ምክር ቤት ስብሰባ ጠርተን አቶ ኃይሉ ሻዎልን ከሊቀመንበርነት ቦታው ማውረድ ይሆናል፡፡ ከዚህም በላይ መኢአድ የሚባል ድርጅት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ከእንግዲህ መኖር አለበት ብለን ስለማናምን ከዚህ በኋላ የኛ ዋናው ስራ መኢአድን እንደ ድርጅት ማፈራረስ ይሆናል፡፡ የመኢአድ በርካታ አመራር አባላት በአሁኑ ወቅትም ቀስተ ደመናን ለመቀላቀል ጥያቄ እያቀረቡ ስለሆነ ከእንግዲህ ለእኛ መኢአድን ማፍረስ ቀላል ስራ ነው፡፡ ስለዚህ እባካችሁን - ንዴታችሁንና ቁጭታችሁን ለጊዜው ዋጥ አድርጉትና ለቅንጅቱ ህልውና ስትሉ ይህንን መፍትሔ ተቀበሉን፡፡” በማለት ዶ/ር ብርሃኑ ጥልቅ የሃዘንና የቁጭት ስሜት ውስጥ ሆነው ጠየቁን፡፡ ፕ/ር መስፍን በወቅቱ ዝም ብለው ከማዳመጥ በስተቀር ምንም አይነት ተጨማሪ አስተያየት ስላልሰጡ ይህንን የዶ/ር ብርሃኑን ሃሣብ ምን ያህል እንደሚጋሩት ወይንም ቀድመው አብረው እንደመከሩበት እስካሁን አላውቅም፡፡ እኔና አቶ ሙሼ የዶ/ር ብርሃኑን ሃሣብ በጥሞና ካዳመጥን በኋላ “ብዙ ጊዜ ሊያጠፉን ፈልጐ ያልተሣካለት መኢአድ ዛሬ ቅንጅቱን ተገን አድርጐ እኛን የማዳከም እድል አግኝቷል፡፡ ይህንን ድርጅት ምን ያህል በውል እንደተረዳችሁት አሁንም ወደፊት በተግባር የምናየው ይሆናል፡፡ ለሁሉም ቅንጅት ፈረሰ ተብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚያዝን ያላችሁትን ሁሉ ተቀብለናል” ብለን ፈቃደኝነታችንን ገልፀንላቸው ወጣን፡፡ ከዚያም በዚያን እለት ከሰዓት በኋላ መኢአድ እንዲለቀቅለት የጠየቃቸውን የምርጫ ክልሎች ሁሉ ኢዴአፓ-መድህን ለቆ ቅንጅቱ ከመፍረስ ተረፈ፡፡ ነገር ግን ለምርጫ ቦርድ አቤቱታ የማቅረቢያው ጊዜ እሮብ እለት ካለፈ በኋላ ኢንጂነር ኃይሉ ሻዎልን ከሊቀመንበርነታቸው ለማንሳት መሞከር ይቅርና በጣም በሚያስገርምና እንቆቅልሽ በሆነ ሁኔታ መኢአድና ቀስተዳመና አዲስ ፍቅር መስርተው ኢዴአፓ-መድህንን በጋራ የማፍረስ ስልታዊ ዘመቻ ጀመሩ፡፡ ሚናችን ሁለቱን ድርጅቶች አሸማግለን አብረው እንዲሰሩ ለማድረግ ነው በማለት ቅንጅቱን የተቀላቀሉት የቀስተዳመና ሰዎች እጩዎችን የማስመዝገቢያ ጊዜው ካለፈ በኋላ በቅንጅቱ ውስጥ ዋና የስልጣን ተሻኳች ሆነው ብቅ አሉ፡፡ ዶ/ር በርሃኑ ከላይ በገለፅኩት መልኩ ፕ/ር መስፍን ቤት ለእኔና ለአቶ ሙሼ ያቀረቡልንን ሃሣብ በአሁኑ መፅሐፋቸው ውስጥ በሚያሳዝን ሁኔታ አንሻፈውና አጣመው በሚከተለው መልኩ አቅርበውታል -፡፡

"--- በመጨረሻም በእኛ እምነት እነኝህ ድርጅቶች እንደድርጅት መኖር እንደሌለባቸው፣ በዚህ እስከ ቀጠለ ድረስ ችግሮች እንደማይጠፉ፣ ስለዚህም ዋና ተግባራችን መሆን ያለበት ቅንጅትን ማዋሃድና የየድርጅቶቹን የግል ህልውና ማጥፋት እንደሆነ፣ ይህ ሲሆን ብቻ እንደሆነ መኢአድ 'መጥፋት' የሚችለውና ከዚያ ጋር ተያይዞ የመጣው ድርጅታዊ ባህል ጠፍቶ በአዲስ መንፈስ መንቀሳቀስ የሚቻለው የሚል ገለፃ አደረግን፡፡ ከብዙ እጅ መጠምዘዝ በኋላ እነ ልደቱም እሺ ብለውን በአምስቱ ቦታዎች ላይ እንደገና በላዕላይ ምክር ቤቱ ውይይት ተደርጐበት ከአምስቱ ውስጥ ሦስቱ ቦታዎች ለመኢአድ ተሰጥተው ችግሩን እልባት ሰጠነው፡፡" (ገፅ 244)

መቼም አንብቦ መረዳት ለሚችል ለማንኛውም ሰው ይህ የዶ/ር ብርሃኑ አባባል ተለባብሶ የቀረበ ውሸትና እውነት የተደበላለቀበት መሆኑን ለመገንዘበ የሚያስቸግር አይመስለኝም፡፡ በዚያን የቅንጅቱ ህልውና መቀጠልና አለመቀጠል በኢዴአፓ-መድህን እጅ በነረበረበት ወቅት ዶ/ር ብርሃኑ ደፍረው ሁለታችሁም ድርጅቶች (መኢአድና ኢዴአፓ-መድህን) መጥፋት አለባችሁ ብለው ደፍረው ሊናገሩ እንደማይችሉ ለማንም ግልፅ ነው፡፡ በአጠቃላይ ዶ/ር ብርሃኑ እውነቱን በትክክል በመፃፍ ያኔ ለቅንጅቱ ህልውና ስንል ኢዴአፓ-መድህንን አታለነዋል ከማለት ይልቅ መዋሸትን እንደመረጡ ለማንም ጥሩ አንባቢ ግልፅ ይመስለኛል፡፡ ሆኖም እሬጨዎችን የማስመዝገቢያው ጊዜ ሙሉ በሙሉ ከተጠናቀቀ በኋላ "ቀስተዳመናና መኢአድ አንድ ላይ ሆነው ኢዴአፓ-መድህንን የማጥፋት ዘመቻ መጀመራቸውን በሚመለከት ቀደም ሲል የገለፅኩትን ሃሣብ አንባቢ በቀላሉ ለመረዳት የሚቸገር ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን ዶ/ር ብርሃኑና ቀስተዳመና ቅንጅትን በበላይነት ለመቆጣጠር ምን ያህል ደባ እንደፈፀሙ በዚህ ፅሁፍ ቀሪ ክፍሎች የምናየው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ገና ከመጀመሪያው ቀስተደመና ሁለቱን ድርጅቶች የማጥፋት ፍላጐት እንደነበረው እራሳቸው ዶ/ር በርሃኑ በመፅሐፋቸው ውስጥ በግልፅ ያሰፈሩትን የሚከተለውን አባባል ማንበቡ በቂ ግንዛቤ የሚሰጥ ይመስለኛል፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ እንዲህ ይላሉ ---

"--- የቀስተዳመና ሰዎች እነዚህ ድርጅቶች (መኢአድና ኢዴአፓ-መድህን) እንደ ድርጅት እስከቀጠሉ ድረስ ቅንጅቱ ሁሌም ችግር ውስጥ እንደሚቆይ፣ ይህ ብቻ ሳይሆን በእነኝህ ድርጅቶች ውስጥ የተንሰራፋው የድርጅት ውስጥ ባህል በፍፁም ጤናማ እንዳልሆነ፣ ስለዚህም ይህን ችግር ከተሻገርን በኋላ በተቻለ ፍጥነት ድርጅቶቹን ማዋሃድና ቅንጅቱን ከአራት ፓርቲዎች ወደ አንደ ፓርቲ መቀየር ምንም አማራጭ የሌለው መንገድ መሆኑን ተገነዘብን፡፡" (ገፅ 243)

ይህ ግልፅ አባባል ከዚያ በኋላ በቅንጅት ውስጥ የነበሩት ሽኩቻዎች የማጥፋትና ያለመጥፋት የህልውና ግብግቦች እንደነበሩ በተጨባጭ የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን ኢዴአፓ-መድህን በጐ ስራ ስለሰራ ለምን ከመኢአድ ጋር ተደምሮ እንዲጠፋ እንደተፈረደበት፣ እነ ዶ/ር ብርሃኑስ በምን የሞራል ብቃት ትግል ውስጥ በገቡ ሦስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ስንት የሕይወት፣ የአካል፣ የኑሮ፣ የጊዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ መስዋዕትነት የተከፈለባቸውንና በአንፃራዊ ድርጅታዊ ጥንካሬአቸው ቅንጅትን ቅንጅት ያደረጉትን ሁለት አንጋፋ ፓርቲዎች እንደጨረቃ ቤት በቀላሉ ለማፍረስ እንደወሰኑና ይህንን በድፍረት ለመናገር መብቃታቸው ለማንም የፖለቲካ ሀሁ ለቆጠረ ሰው የሚዋጥለት አይመስለኝም፡፡ በሂደት ሁሉንም ነገር ለመረዳት እንደቻልነው ቀስተዳመናና መኢአድ በዚያን ወቅት አንድ ላይ ቆመው መጀመሪያ ኢዴአፓ-መድህንን ለማጥፋት የሞከሩት ያለ በቂ ምክኒያት አልነበረም፡፡ ሁለቱም ድርጅቶች አንዳቸው በሌላቸው ላይ የበለጠ ብልጥ እንደሆኑ አድርገው በማሰብ በደረሱበት የየራሳቸው ቀመር ኢዴአፓ-መድህንን ቀድሞ ማጥፋቱ ተመራጭ ስልት እንደሆነ በማመናቸው ነበር፡፡ እነ ዶ/ር ብርሃኑ መጀመሪያ ከመኢአድ ጋር አብሮ በመቆም የተሻለ ብልጠት አለው ብለው የሚያስቡትን ኢዴአፓ-መድህንን ማጥፋት ከቻሉ ከዚያ በኋላ የየዋህነት ፖለቲካ ያራምዳል ብለው የሚያስቡትን

መኢአድን ማዳከም የቀለለ እንደሚሆን ገምተዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ መኢአድ ድርጅታዊ መሠረት ያለውንና ለእኔ አርፎ የማይተኛልኝን ኢዴአፓ-መድህንን በቅድሚያ ከነዶ/ር ብርሃኑ ጋር ሆኜ ካዳከምኩ በኋላ ምንም አይነት ድርጅታዊ መሠረት የሌላቸውንና የፖለቲካ ተንኮሉን የማያውቁበትን ቀስተዳመናዎችን በቀላሉ ከፖለቲካ መድረኩ ማስወገድ እችላለሁ ብሎ ገምቷል፡፡ እንግዲህ ሁለቱን ድርጅቶች በጋራ እንዲቆሙ ያደረጋቸው ይህ ኢዴአፓ-መድህንን ቀድሞ የማጥፋት ፍላጐት እንጂ እነርሱ እርስ በርሳቸው የተሻለ ፍቅርና የዓላማ አንድነት ኖሯቸው አልነበረም፡፡ ሁለቱ ድርጅቶች ተሳክቶላቸው ኢዴአፓ-መድህንን አጥፍተው ቢሆን ኖሮ ዛሬ በውጭ አገር የሚገኙት ደጋፊዎቻቸው በመኢአድና በቀስተዳመናነት ተከፋፍለው እርስ በርስ መናቆር እንደጀመሩት ሁሉ እነሱም እርስ በርስ ለመጠፋፋት ጊዜ አይወስድባቸውም ነበር፡፡ እንግዲህ ይህንን በቅንጅት ውስጥ የነበረን ሴራና ደባ በውል ሳይገነዘቡ ነበር አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች እነዚህ ድርጅቶች አድመው ህልውናቸውን ሊያጠፉት ሲሞክሩ ለምን ዝም ብላችሁ እጃችሁን አጣጥፋችሁ አልጠፋችሁም በሚል የፖለቲካ የዋህነት በኢዴአፓ-መድህን ላይ ተገቢ ያልሆነ ፍርድ ሲሰጡ የሚደመጡት፡፡

በአጠቃላይ በእዚህ የጽሁፍ ክፍል ውስጥ እንዳየነው ከነችግሮቻቸውም ቢሆን የቅንጅቱ አንፃራዊ ድርጅታዊ ጥንካሬ ምንጭ የሆኑት ሁለቱ ድርጅቶች ማለትም መኢአድና ኢዴአፓ-መድህን ናቸው፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን ሃቅ አምነው መቀበል ቢሳናቸው እንኳ የቅንጅቱ ድርጅታዊ ጥንካሬ በእኔና በቀስተዳመና ነው የመጣው ብሎ አይን ያወጣ የታሪክ ሽሚያ ውስጥ ከመግባት ይልቅ ቢያንስ የቅንጅቱ ጥንካሬ "የጋራችን ነው" ብለው ቢናገሩ የተሻለ ክብር የሚያሰጣቸው አባባል ይሆን ነበር፡፡ ስለዚህ የግንቦት 97ቱ የምርጫ "ውጤት" የተገኘው በአስተሳሰብ ጥራትና በድርጅታዊ ጥንካሬ ነው ከተባለ - ውጤቱ ቢበዛ የኢዴአፓ-መድህንና የመኢአድ፣ ቢያንስ ደግሞ የሁሉም የቅንጅት አባል ድርጅቶች የጋራ ውጤት ከመሆን አልፎ ዶ/ር ብርሃኑ በመፅሐፋቸው እንዳተቱት የእሳቸውና የቀስተዳመና ብቸኛ ውጤት የሚሆንበት ምንም አይነት አሳማኝ ምክንያት አይኖርም፡፡

ይቀጥላል….